
በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



ከኖቬምበር 11-20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከኖቬምበር 21-30፣ ከዲሴምበር 1-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ


ኖቬምበር 2026

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፤ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ23 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡


በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 43.2-77.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች አዶላ 77.6፣ ብላቴ 59.4፣ ማይጨዉ 56.8፣ ያቤሎ 56.7፣ ጽጌሬዳ 55.3፣ ኮንሶ 54፣ ሰመራ 51፣ በደሌ 49.8፣ አዲግራት 44፣ ቡሌ ሆራ 43.8፣ ወላይታ ሶዶ 43.3፣ ሳዉላ 43.2 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡




ምስል1: ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ እና ዶሎ ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሪ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ10-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)። በተጨማሪም የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች ዋግህምራ፣ ሰሜን ወሎ ዞኖች፤ የቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ የምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ እና ባሌ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች፤የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሐሁሲ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች ከ10-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ዝናብ ከ3-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ቆራሂ፣ ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ጊዶሌ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)።



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም ሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፤ በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በሌላም በኩል አልፎ አልፎ ሰብል በደረሰባቸው በሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛው የሃገሪቱ ስፍራዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመጠኑም ቢሆን አሉተዊ ተፅእኖ ነበረው (ካርታ 4)።

1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ላይኛውና መካከለኛው አባይ እንዲሁም ላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት አግኝተዋል፡፡ በተለይም በመካከለኛውና ታችኛው አሞ ጊቤ፣ ላይኛው ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ላይኛው አባይ እንዲሁም በላይኛው ተከዜ የተወሰኑ አካባቢዎች በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ የአፈር እርጥበትና የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንዲጠናከር እንዲሁም ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ግብዓት ጥሩ አስተዋፅየ እንዳደረገ የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ተከዜ፣ በታችኛው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በታችኛው ዋቤ ሸበሌና አጋዴን ተፋሰሶች የተወሰኑ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበረ ሲሆን፣ ይህም ለአካባቢያዊ የውሃ ሁኔታ ውስን መሻሻል አስገኝቷል (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አከባቢዎች ላይ በሂደት እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ በመጠንም እና በስርጭት የተሻለ ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡ ፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2026 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2026 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች		
ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን
አሮሚያ	የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ናጎብ፣ ጀረር ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ጌድዮ፣ ወላይታ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች		
አሮሚያ	ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ የባሌ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የምስራቅ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ እና የአዊ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	የካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	የአኝዋክ፣ መኾርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)

ደቡብ ኢትዮጵያ	የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ትግራይ	ምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች	ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሁሉም ዞኖች		ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10 ሚ.ሜ)

2.2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 8)፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆንና፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።



ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ በመጠንም እና በስርጭት የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)።

2.4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በስምጥ ሸለቆ፣ በአሞ ጊቤ እና በላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንደሚኖር ይጠበቃል። የሚጠበቀውን የእርጥበት ሁኔታ በአግባቡ ለመጠቀም በየተፋሰሶቹ ከታች የተዘረዘሩትን ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች			
ከቀላል እስከ መካከለኛ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የተሰጠ ምክረ ሃሳብ**
ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ጃረር፣ ዞኖች **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ገዲዬ፣ አማሮ፣ ወላይታ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች የሲዳማ ክልል ሁሉም የክልሉ ዞኖች	➢ በጋ ተጠቃሚ በሆኑ ደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ➢ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት	➢ በጥቂት ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ➢ የእርጥበት ትነት መኖር	➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ➢ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች የአረም ማስወገድ ስራዎችን መስራት ➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤

ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚ ጠበቅባቸው ዞኖች			
ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የተሰጠ ምክረ ሃሳብ**
ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ኦሮ ጉደሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ የባሌ ዞኖች የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የምስራቅ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ እና የአዊ ዞኖች የካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኝዋክ፣ መኾንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች	➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መኖር እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ በክረምቱ መጨረሻ ላይ ለተዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች ፍሪ ለማፍራት ➢ ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ➢ ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፈላጎት ማሟላት ➢ በበጋ መስኖ ለሚከናወን የግብርና እንቅስቃሴ	➢ በደረሱ የመኸር ሰብሎች የሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖር ➢ ከእርጥበትና ሙቀት የተነሳ የዋግ በሽታ መከሰት	➢ የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን ➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ ➢ የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• ስምጥ ሸለቆ • ኦሞ ጊቤ • ላይኛው ባሮ አኮቦ • በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ	• የወንዞችና የግድቦች የውሃ መጠን መጨመር • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ የውሃ ክምችት መሻሻል • የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መጨመር	• የአፈር መሸርሸርና የደለል ስጋት • የፍሳሽ መውረጃዎች ቆሻሻ መዘጋት	• የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና የግድቦችን የውሃ መጠን መከታተል፤
ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ታችኛው ኦሞ ጊቤ • ስምጥ ሸለቆ • ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌና ኦጋዴን • በጥቂት የአባይ ተፋሰሶች ላይ	• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል • የወንዞችና የትናንሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎች መጠነኛ መሙላት	• የፍሳሽ መውረጃዎች መዘጋት	• የውሃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም • የፍሳሽ መውረጃዎችን ማፅዳት
ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ተከዜና መረብ ጋሽ • አዋሽ • አፋር ዳናክል • ላይኛው ዋቤ ሸበሌ	• የጎርፍና የደለል ስጋት አለመኖር	ከፍተኛ ትነት	• የሚገኘውን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም • መጠነኛ የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና ከብክነትና ከብክለት መከላከል • ለደረቅ ወቅት የውሃ አቅርቦት መዘጋጀት